# ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገር እድገት የሚኖራቸው ሚና

ብርሃኑ ነጋ

ሕዳር 12 ቀን 1996 ዓ.ም.
በአምስተርዳም ከተማ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

<u>ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገር እድገት የሚኖራቸው ሚና</u>

I. *መግቢያ:-*

***በመጀመሪያ አገራችን አሁን ባለችበት ሁኔታና ከፊቷ በተደቀኑት ችግሮች ላይና እነኝህን ችግሮች ለመቅረፍ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ በሚመለከት ያለኝን አስተያየት እንዳቀርብ በአምስተርዳም የኢትዮጵያውያን ማህበር ስለጋበዘኝ በጣም አመሰግናለሁ::***

II. *አገራችን አሁን ያለችበት ሁኔታና ከፊቷ የተጋረጡ ችግሮች*

*አገራችን አሁን የምትገኝበትን ውጥንቅጥ ሁኔታ ለመቃኘት መለስ ብለን ላለፉት ብዙ አመታት የሆኑትን አሁን ካለው ሁኔታ ጋር በማጣመር መመልከት **ይኖርብናል**:: ለዚህ እንዲረዳ የአገራችንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገፅታ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ባለፉት አራት አስርት አመታት በጣም በአጭሩ ለመመልከት **ልሞክር**:: በእኔ ግምት የአገራችን ውስብስብ ችግሮች ከሶስት መሠረታዊ ጉዳዩች ጋር የተያየዙ ናቸው ብዬ ስለማምን የማቀርበውን **በጣም** አጭር **ዘገባ** በነኝሁ ሶስት ጉዳዩች ላይ እንዲያጠናጥን አደርጋለሁ::እነኝህም*

*1ኛ) አስተሳሰብ*

*2ኛ) አስተተዳደርና*

*3ኛ) ካፒታልና አጠቃቀሙ ናቸው*

*ከዚህ አንፃር አገራችን ምን ገፃታ አላት?*

## I. 1. *የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዋና ማህበራዊ ሁኔታ:-*

***የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ አጠቃላይ ሂደት ለመዳሰስ ጥሩ አመላካች የሚሆነው አህዝ አጠ ቃላይ የኢኮኖሚ እድገቱና ከዚህ ጋር የተያያዘው የህዝቡ አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ ነው:: ይህ ገቢ በየአመቱ የሚያሳየው እድገት የህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ኑሮ እየተሻሻለ ለመምጣት መቻል አለመቻሉን በቅጡ ያመለክታል:: በዚህ አህዝ መሠረት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላለፉት አራት አስርት ዓመታት በዓመት በአማካይ በ*2.6%* አድጓል:: በዚያው መጠን ግን የህዝብ ብዛት በዚህ ጊዜ ትንሽ ከ*2.6%* በላይ እያደገ መጥቷል:: ይህም በመሆኑ የህብረተሰቡ አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ በዚያን ጊዜ ከነበረበት ምንም ፊቅ***



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

አለማለቱ ብቻ ሳይሆን፣ አሁን እንዲያውም ትንሽ ዝቅ ብሏል። አገራዊ አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ (በ1973 ቋሚ የብር መግዥያ አቅም) በ1953 228 ብር፣ በ1957 ደግሞ 257 ብር ሲሆን ይህ አሀዝ በ1994፣ 261 ብር፣ በ1995 ደግሞ 244 ብር ብቻ ነው።

በዚህ ረጅም ጊዜ የኢኮኖሚያችን አወቃቀርም ይህ ነው የሚባል ለውጥ አላመጣም። አሁንም እንደያኔው በጣም ብዙው ህዝብ ኑሮውን የሚገፋው ፍፁም ኋላ ቀርና ተፈጥሮን እንዳለ ተቀብሎ መሠረት ባደረገ የግብርና ኢኮኖሚ አማካይነት ሲሆን፣ እንዲያውም የሰው ብዛት እየጨመረ በሄደ ቁጥር የዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ አማካይ የነፍስ ወከፍ ምርት ከዓመት ዓመት እየቀነሰ በመምጣቱ ይህችኑ ኑሮ ኑሮ ብሎ መኖር የማይችልበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ነው። የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ አማካይ የነፍስ ወከፍ ምርት ላለፉት 42 ዓመታት በዓመት በ 1.2% እየቀነሰ መጥቷል።

እጅግ በጣም መሠረታዊ በሆነው እንዲያው ለመኖር የሚያስፈልገውን ምግብ ለማግኘት ያልቻለው ህዝባችን ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መሄድ ለገጠሬው ህዝብ ኑሮ እንዴት እያደር እንቆቅልሽ እየሆነበት እንደሄደ መገንዘብ አያዳግትም። በአፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን በተከሰተው ትልቁ ችጋር (1965) እራሱን መመገብ ያቃተው ህዝብ በከፍተኛው ስሌት ወደ 1.5 ሚልዮን ህዝብ፤ ችጋሩ የዳሰሰው የአገሪቱም ክፍል በአብዛኛው ሰሜኑን ብቻ የነበረ ሲሆን እጅግ ትልቅ በተባለው የ1977 የደርግ ጊዜ ችጋር የስርጭት አድማሱን ወደ ምስራቁም ክፍል በማስፋት ወደ 6 ሚሊዮን ህዝብ አጥቅቷል። ዛሬ በዘንድሮው ድርቅ ምክንያት እራሱን መመገብ ያቃተው ገበሬ ቁጥር ወደ 14 ሚሊዮን ያሻቀበ ሲሆን፣ ምንም ድርቅ በሌለበት በሰላሙ ጊዜ ለመኖር የእህል እርጥባን የሚጠብቀው ገበሬ ቁጥር በየዓመቱ 6 ሚሊዮን ደርሷል። ለዘመናት ያልተቀየረ ባህላዊ የአስተራረስ ዘዴ በየጊዜው እየጨመረ ከሚመጣው የሕዝብ ብዛት ጋር ተዳምሮ አንዳንድ አካባቢዎችን በፍፁም ለመኖር የማያመቹ ቦታዎች አድርጓቸዋል። በ1965ቱ ችጋር ጊዜ የገጠሩ ህዝብ ብዛት ወደ 29 ሚሊዮን ይገመት ነበር። ዛሬ ይህ ቁጥር በእጥፍ አድጐ ወደ 58 ሚልዮን ደረሷል።

የኢኮኖሚ ድቀት ውጤት ኢኮኖሚ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። ከዚያ አልፎ በፖለቲካና በማህበራዊ ህይወታችን ላይም የሚያመጣው ምስቅልቅል እጅጉን ወደ ባሰ የድህነት አዙሪት ውስጥ መክተቱ በፍፁም የማይቀር ነው።



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

በ1960ዎቹ የነበረው አንፃራዊ ኋላ ቀርነት በተለይም የ1965 ችጋር ያስከተለው አገራዊ የመዋረድ ስሜት በጊዜው ከነበረው ልሂቅ ደካማነትና መጠነኛ ለውጥ እንኳን ለማምጣት ችሎታ ከማጣት ጋር ተዳምሮ የ1966ቱን አብዮት አምጥቷል:: መለስተኛ መሻሻል (reform) ለማምጣት ባለመቻሉም ልሂቁ የለውጥ እንቅስቃሴውን እጅግም ላልተብላሉ ፅንፈኛ አስተሳሰቦች ትቶ ማህበረሰቡን ለ66ቱ ማህበራዊ ነውጥ፣ ብሎም ዘግናኝ ለሆነ ወታደራዊ አገዛዝ አሳልፎ ሰጠው:: የዚህም አገዛዝ የ17 ዓመታት ዕድሜ ድህነትንና ችጋርን ብቻ ሳይሆን ከነኝህም የከፉና ዘላቂ የሆነ፣ እስከአሁንም ልናሽረው ያልቻልነው የሥነ ልቡና ቁስል ትቶልን አልፎአል::

ይህንን ክፉ ጊዜ በአገር ደረጃ በጋራ መቋቋም ማቃቱ በሰላሙም ጊዜ ከነበሩ መለስተኛ ብሄራዊ ብሶቶች ጋራ ተዳምሮ ለችግሮች አገራዊ ሳይሆን ጐሳዊ መፍትሄ ለመፈለግ ለተነሱ ሀይሎች ጉልበትን ሰጠ:: ይህም በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን አንድነት በመጠኑም ቢሆን ሸረሸረው:: ይህ ሁሉ ምስቅልቅል የፈጠረው በአገር ላይ እምነት ማጣት በንጉሱ ጊዜ እንደ ውርደት ይቆጠር የነበረው ስደት ሁሉም ሰው የሚመኘውና የሚናፍቀው አገራዊ ክስተት ሆነ:: ከዚህም በላይ፣ እየከፋ የመጣው ድህነትና ክፉ አስተዳደር ከነባሮቹ ኋላ ቀር ባህላዊ ገፅታዎች ጋር ተደማምረው በፊትም በመጠኑ የነበሩ፣ ግን በዘመናዊ ትምህርት እድገት፣ በተለይ በከተሞች አካባቢ እየተዳከሙ የነበሩ አስከፊ ባህላዊ አካሄዶች በማህበረሰባችን ስነልቦና ሰፋ ያለ ይዞታ እንዲኖራቸው አደረጉ:: ምቀኝነት፣ ጨለምተኝነት፣ ተስፋ መቁረጥና በራስ አለመተማመን በፍፁም ለብልፅግናና ለእድገት የማያመቹ ግን በማህበረሰባችን ስር የሰደዱ የሥነልቡናዊ ቁስል ሰንኮፎች ሆኑ::

ስለሆነም አሁን ባለንበት ሁኔታ ከላይ የጠቀስኳቸው በደርግ ጊዜ የተንሰራፉ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ምስቅልቅሎች በደርግ ጊዜ የነበሩትን ያህልም ባይሆኑ በመሠረቱ ተቀርፈዋል ማለት አይቻልም:: የመንግሥት ፍፁም የበላይነት እየሳሳ ሳይሆን እንዲያውም እየተጠናከረ የመጣ ይመስላል:: ኢሕአዴግ ከ12 ዓመታት በኋላ አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል በመሠረቱ ትክክልና ፍትሀዊ ነው ብሎ የሚያምንበትን ዴሞክራሲያዊ የአስተዳዳር ስርዓት በአገሪቱ መመስረት ተስኖታል:: ከዚያም አልፎ ደርግ በጭካኔ ቀጥቅጦ በፍርሀት ቀንበር ውስጥ የከተተው ሰብዕናችን ከተደበቀበት ሽል ውስጥ እስከአሁንም መውጣት አልቻለም:: የወደፊት ሕይወታችንም ውጤት በአብዛኛው ይህንን ውስጣዊ ነፃነት ማግኘት በመቻልና ባለመቻላችን መካከል የተንጠለጠለ ይመስለኛል::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

በመሆኑም ይህ ሁኔታ አሁን በሚሄድበት ከቀጠለ በሰላም የመኖር ህልማችን ራሱ ጥርጣሬ ውስጥ ይገባል። የድህነት መክፋት አሁን ከተፈጠረው የእርሰ በርስ መጠራጠር ጋር ተዳምሮ ለችግሮቻቸው ከኢትዮጵያዊነት ውጪ መፍትሄ ለመሻት ለሚፈልጉ በታች ህይሎች ጉልበት ሊሰጣቸው እንደሚችል አለመገመት ከታሪክ አለመማር ነው። ከዚህም አልፎ የድህነቱ ጥልቀት መጠን እየጨመረ በሄደ ቁጥር አብሮት የሚዳብረው ጨለምተኝነትና ተስፋ መቁረጥ ለሁሉም አይነት የህይማኖት አክራሪዎች መራቢያ ጥሩ ሜዳ ነው የሚሆንላቸው። ይህም እንደ አገር ስንኮራበት የነበረውን በሀይማኖቶች መሀከል የቆየውን መከባበርና በሰላም አብሮ መኖር ክፉኛ እንደሚፈታተነው መጠራጠር አይቻልም ። አተኩሮ ለሚመለከተው የዚህ ሂደት አመላካቾች በማህበረሰባችን ውስጥ አሁንም በሰፊው ይታያሉ። ምናልባትም በአሁኑ ጊዜ ከምንም በላይ በእጅጉ እየተጠናከረ የሄደውና እንዲያውም እንደ አደገኛ ፉክክር የተያዘው የማምለኪያ ቦታዎችን በብዛትና በስፋት ለመስራት የሚደረገው መሯሯጥ ነው። አለማዊው ኑሮ ፍፁም ግራ የሚያጋባ ጨለማ ሲሆን መፍትሄ ለመሻት ወደ አማልክቶች መመልከት የተለመደ የሰው ልጆች አካሄድ ነው። ምናልባትም በዚህ ዙሪያ በተለያዩ የሰው ልጆች መሀከል ያለው ልዩነት በአንድ በኩል ወደ ፈጣሪ መመልከት ዓለማዊ ህይወታቸውን ለማሻሻል ለሚያደርጉት የእለት ተዕለት የማያቋርጥ ትግል መነፈሳዊ ድጋፍ እንዲሰጣቸውና እንዲያጠናክራቸው በሚሹት እና በሌላ በኩል መንፈሳዊ ህይወትን ከዓለማዊው ህይወት መሸሸያ እና መደበቂያ፣ ዓለም ለስኬት የምትፈልገውን ትጉህ ስራ ለመስራት የሰነፉ ደካሞች መጠለያ አድርገው በሚወስዱ መካከል ይመስለኛል። በሁለቱም መሀከል በሰማይ ቤት የሚኖራቸውን አቀባበል መተንበይ ባይቻልም በምድር ኑሮአቸው ግን የቀድሞዎች ከኋለኞቹ የተሻለ አጠ ቃላይ አለማዊ ኑሮ እንደሚኖሩ አያጠራጥርም።

ይህ ከላይ የሳልኩት የጨለማ ህይወት ሊሻሻል ይችላል? በእኔ እምነት በጣም ይቻላል ባይ ነኝ። ይህ እንዲሆን ግን ከላይ ችግሮች ናቸው ባልኳቸው ጉዳዮች ማለትም በአስተሳሰባችን፣ በአስተዳደራችንና በካፒታል ማከማቸትና ያከማቸነውንም ካፒታል በአግባቡ መጠቀም በመቻላችን ላይ ይወሰናል እላለሁ። በነዚህም አስፈላጊ ለውጥ ውስጥ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚኖራቸውን ሚና ከመግለፄ በፊት ግን መለወጥ አለባቸው የምላቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች ላንሳ።

ወደሚቀጥለው ርዕስ ከማምራቴ በፊት ግን፣ አሁን ላለንበት ሁኔታ ማነው ተጠያቂው ለሚል በአዕምሯችሁ ለሚጉላላ ጥያቄ አጭር መልስ ሰጥቼ ልለፍ። ለዚህ እኔ ያለኝ መልስ በጣም ቀላል ነው። ሁላችንም የሚል ነው። የ66 ነውጥ ፅንፈኛ መስመር እንዲይዝ



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

የገፋፉት ምሁራን የሚወቀሱትን ያህል የጃንሆይ መንግሥት ለዘብተኛ ለውጥ እንዲያመጣ መገፋፋት ያቃተቸውን የቅድመ አብዮት ልሂቃን፣ የደርግን ዘግናኝ ጭፍጨፋ ለመከላከል አንድ ቃል መተንፈስ የተሳናቸው የህይማኖት መሪዎቻችን፣ ባጠቃላይም ይህ ሁሉ ግፍ ሲፈፀም እኔጋ እስኪደርስ ዝም ማለት ይሻለኛል ብሎ የሆነውን ማየት ብቻ የመረጠ ሁሉ ከታሪክ ተወቃሽነት የሚድኑ አይመስለኝም፡፡ የታሪክ ተወቃሽነትን የሚያመጣው ክፉ ድርጊት ማድረግ ወይም የክፉ ድርጊት ተባባሪነት ብቻ አይደለም፣ ክፉ ድርጊት እንዳይመጣ ለመከላከል ቁርጠኛነትና ፍላጐት ያልነበራቸውም ይጠየቃሉ፡፡ ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታ ይህን ያህል ከልኩ ስለዚህ ስብሰባ ዋና ጭብጥ ርዕስ ልመለስ፡፡

## የተሻለ ህይወት ለማምጣት ምን ማድረግ አለብን ?

የአገር ኢኮኖሚ እድገት ግለሰቦች ህይወታቸውን ለማሻሻል የሚያደርጉት ጥረት ድምር ውጤት ነው፡፡ ስለሆነም ፈጣን እድገት ለማምጣት የግለሰቦችን ተነሳሽነት የሚገፋፉና የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ ተቋሞችና አሰራሮች ያስፈልጋሉ፡፡ ከዚያም በላይ ግን ግለሰቦች ጥረታቸው በህይወታቸው ላይ ሁነኛ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል ብለው ማመን አለባቸው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ከዐቅማቸው በላይ የሆኑና ሊቆጣጠሯቸው የማይችሉ ኃይሎች (መንግሥት፣ እግዚአብሄር፣ ወዘተ) በሕይወታቸው እርምጃ ላይ ተፅእኖ ሊኖራቸው እንደሚችል ቢቀበሉም በዋናነት የራሳቸው ጥረትና የመሻሻል ፍላጐት የወደፊት ሕይወታቸንን ይወስናል፣ እነኝህ ኃይሎችም "ይረዱናል፣ ያጠናክሩናል እንጂ እንቅፋት አይሆኑብንም" ብለው ሊያምኑ ይገባል፡፡ ማለትም ተስፋ ያላቸውና የራሳቸው ህይወት ባለቤት (empowered) የሆኑ ግለሰቦች አብዛኛውን የሕብረተሰብ ክፍል ሲይዙ ነው እድገት፣ በተለይም የከበርቴ ሥርዓት እድገት፣ ሊመጣ የሚችለው፡፡ እንዲህ አይነት ነፃነት የሚሰማቸው ግለሰቦች በበዙበት አገር የሕዝቦችን የጋራ ህይወት ለማመቻቸትና በሰዎች መሀከል የሚነሱ ልዩነቶችን ለመዳኘት የተቋቋሙ እንደ መንግሥት ያሉ ተቋሞች በግለሰቦች እንቅስቃሴና መብት ላይ ያላቸው ተፅእኖ በጣም የተመጠነ ነው፡፡ አንዳንዴ ያላቸውን የስልጣን ገደብ በቅጡ ባለመገንዘብ የሰዎችን ነፃነት ለመቆንጠጥ ሲሞክሩም ህይለኛ ተቃውሞ ስለሚገጥማቸው መንግሥቶቹም ይህንን ተቀብለው ማህበረሰቡ በፈቀደው ሥልጣን ዙሪያ ተገድበው ይኖራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ሰዎች በአብዛኛው ልበ ሙሉ ናቸው፡፡ የመፍጠር ችሎታቸውን (creativity) በሰፊው ይጠቀማሉ፡፡ ራሳቸውንና ሕብረተሰባቸውን ይጠቅማል እስካሉ ድረስ አዲስ ሀሳብ የማፍለቅ ወይንም የመቀበል ችሎታቸው ያልተገደበ ነው፡፡ ለዚህም ነው እንደ አማርትያ ሴን ያሉ የኢኮኖሚክስ



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ተመራማሪዎች የሰዎች ነፃነት መስፋት የኢኮኖሚ እድገት ዋነኛ መሳሪያም ግብም ነው የሚሉት፡፡

በአገራችን ለተንሰራፋው የህዝብ የውስጥ ነፃነትና የችሎታ ማጣት ስሜት የተደራረቡ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ምክንያቶች ቢኖሩም በተለይ መፍትሄ ስናስብ በዋናነት ልናየው የሚገባን በአገራችን ለረጅም ጊዜ የተንሰራፋውን የመንግሥትን ቅጥ ያጣ ስልጣን የምንገድብበትን መንገድ ማበጀት ነው፡፡ ለዚህ መነሻው ሕብረተሰባችን ሥለ መንግሥት ያለው አስተሳሰብ፣ መንግሥት ስለ ህዝብና ስለራሱ ስልጣን ያለው እይታ መሠረታዊ በሆነ መልኩ መቀየር ይኖርበታል፡፡ ህዝብ መንግሥትንና የተለያዩ የመንግሥት ተቋማትን እንደ አስፈሪ ጭራቅ ሳይሆን እራሳቸው እንደፈጠሯቸው፣ ለራሳቸው ጥቅም እንደሚውሉ የእድገትና የሰላማዊ ህይወት መሳሪያዎቻቸው ሊያዩዋቸው ይገባል፡፡ የመንግሥት ባለሚሎችም ህዝብን የሚፈሩ፣ የመንግሥት ስልጣንም ፍፁም ጊዜያዊ የሆነ ከሕዝብ የተሰጠ አደራ መሆኑን የተቀበሉ፣ ነገ ይህንን ስልጣን ለሌላ አስረክበው በዚሁ ሕብረሰተብ እንደ ዜጋ የሚኖሩ መሆኑን የሚያውቁና በዚህም ምክንያት የተሰጣቸውን ሥልጣን በአግባቡ የሚጠቀሙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የመንግሥት ሥልጣን በማያወላዳ ሁኔታ በሕዝብ የበላይነት ስር መሆኑ ለሰዎች የውስጥ ነፃነት መዳበር ወሳኝ ሚና ይጫወታል ባይ ነኝ፡፡ የሕዝቡ የውስጥ ነፃነት መፋፋት ደግሞ ለኢኮኖሚ እድገታችን ፍፁም አማራጭ የሌለው መንገድ ይመስለኛል፡፡ የዴሞክራሲያዊ መንግሥት መኖር ለአገር ሰላምና መረጋጋት፣ ለኢኮኖሚ ብልፅግናም አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች መሆናቸው ከአጠቃላይ የሀሳብ መመሪያ ግንዛቤም በላይ ከብዙ አገሮች ተመክሮ በመነሳት አሀዛዊ ድጋፍ የተሰጣቸው ግንኙነቶች ናቸው፡፡ ይህ ግንኙነት በኢትዮጵያም ላይ ተፈፃሚነት እንዳለው ከቶውንም መጠራጠር አይቻልም፡፡ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር በአገራችን መኖሩ ግን ከዚያም በላይ ለብልፅግናችን ፋይዳ አለው እላለሁ፡፡ ይኸውም ከላይ በጠቀስኩት የሕዝባችንን የውስጥ ነፃነት በማበልፀጉ ላይ በሚጫወተው ሚና ነው፡፡ የእውነተኛ ዴሞክራሲ መኖር አንዱና ዋናው መለኪያ ዜጎች የአንድ መንግሥት ስልጣን ላይ መውጣት ምክንያት እነሱ መሆናቸውን ማወቃቸው፣ ማመናቸውና ከዚያም በላይ መንግሥት ከህዝብ ከተሰጠው የስልጣን ገደቡ ለማለፍ ቢያስብ በጋራ ሊያቆሙት መቻላቸውን ማመናቸው ላይ ነው፡፡ ይህ እምነት ነው ለውስጥ ነፃነታቸው ጥንካሬ የሚሰጣቸው፡፡ ይህ የውስጥ ነፃነት ነው ለስራ ተነሳሽነትና አዲስና የተሻለ ነገር ለማምጣት ድፍረትና ወኔ የሚሰጣቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እንዲህ አይነት ነፃነት የሚሰማውን ሕዝብ የሚያስተዳድር ዴሞክራሲያዊ መንግሥት የዜጎችን ነፃነት፣ እንቅስቃሴና ተነሳሽነት ለመገደብ ፍላጐቱም ችሎታውም አይኖረውም፡፡ በዚህም



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ምክንያት የሚያወጣቸው እስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና እነኝህንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣ የአፈፃፀም ስልቶችና የአስተዳደር አኪያሄዶች የዜጐችን ተነሳሽነትና አፍላቂነት እንዲያውም የሚያበረታቱ ይሆናሉ፡፡ እንግዲህ ይህ የግለሰቦች ተነሳሽነትና አፍላቂነት በአንድ በኩልና ይህንን የሚደግፍና የሚያበረታታ ፖሊሲና አስተዳደር በሌላ በኩል ተጻምረው ነው ምርታማነትን ብሎም የኢኮኖሚ እድገትንና ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄደውን ባህላዊና ማህበራዊ ብልፅግናን የሚያመጡት፡፡

ይህ ማለት ግን በምንም መልኩ የሕዝባችን የውስጥ ነፃነት ማጣት ምክንያቱ የፖለቲካ ዴሞክራሲ ማጣት ብቻ ነው ማለት አይደለም፡፡ ለዘመናት የከረመና የተወሳሰበ ችግርን እንደዚህ በቀላሉ ልንገላገለው አንችልም፡፡

ለምሳሌ በእኔ እምነት ለውስጥ ነፃነት ማጣታችን አንዱ ምክንያት ለረጅም ጊዜ አብሮን የቆየው ከሀይማኖታዊ አስተምህሮታችን ጋር የተያያዘውና በዚያም ምክንያት ባህላችን የሆነው ለሕይወት ያለን ጨለምተኛ (Fatalistic) አመለካከት ነው፡፡ ከዛሬ ሰላሳ ዓመት በፊት ፕሮፌሰር መስፍን እንዳሉት፣ ሕይወትን እንደጊዜያዊና ለሞት እንደምንዘጋጅለት መድረክ አድርጐ የሚወስድ፣ ስለዚህም ለአለማዊ ብልፅግናና እድገት እምብዛም ትኩረት የማይሰጥ ባህል በተንሰራፋበት የኢኮኖሚ ብልፅግና (ዓለማዊ) መመኘት ከንቱ ህልም ይሆናል፡፡ ከድህነት ለመውጣት የሚደረግ ጥረት መሠረት የሚያደርገው ድህነት ሊሸሹት የሚገባ መጥፎ ነገር መሆኑን መቀበል ነው፡፡ ዓለምን እንደጊዜያዊ ክስተት፣ አልፎም ለዘላለማዊው ህይወትና ፍሥሐ መግቢያ ፈተና የሚወሰድበት ት/ቤት፣ ድህነትም የሚከላከሉትና የሚሸሹት ሳይሆን ባለበት የሚቋቋሙት የፈተናው ዋና አካል አድርጐ በሚወስድና የዚህ አይነት እምነትና ባህል ስረ በሰደደበት አገር የኢኮኖሚ እድገት ከቶውንም አዳጋች ነው የሚሆነው፡፡ ከላይ የጠቀስኩት የውስጥ ነፃነት ፍላጐት ዓለማዊ ኑሮን ከምር ከመውሰድ የሚመጣ ነው፡፡ የዚህም የውስጥ ነፃነት ውጤት ሕይወትን የመቋቋምና የማሸነፍ ሀይል በእጄ ነው ብሎ ማመን ነው፡፡ ይህም ነው የተባለውን ጥረትና ተነሳሽነት የሚገፋፋውና ለእድገት ጥርጊያ መንገድ የሚከፍተው፡፡ ዓለምን እንደ ክፉ ነገር የሚያይ፣ የዓለምንና የሕዝቧን ብሎም የራሱን ሕይወት ከሱ በላይና ከሱ ቁጥጥር ውጪ ናቸው ለሚላቸው ሀይሎች ሙሉ ለሙሉ ያስረከበ ሰው ነፃነትን ሊሻና ሊናፍቅ፣ ለብልፅግና ሊዳክር ፈፅሞውኑ አይቻለውም፡፡ ይህ ዓይነት አስተሳሰብ የተጠናወተው ሰው ወይም ማኅበረሰብ እድገትን እራሱ አለመመኘቱ ብቻ ሳይሆን ያደጉትንና ለማደግ የሚጥሩትንም በክፉ የሚያይ፣ ስለዚህም የእነሱንም እድገት የሚያሰናክል በቁሙ



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

የሞተ ሰው ወይንም ማህበረሰብ ነው። እንደዚህ አይነት አስተሳሰብ ባለበት ሁኔታ ድህነት እየጨመረ መሄዱ አያስገርምም። እንዲያውም የድህነት መጨመር እንዲህ አይነቱን አስተሳሰብ እያጠናከረውና እያጐለበተው ማኅበረሰቡን ወደባሰ የድህነት አዙሪት ውስጥ ይከተዋል። ወደፊት ህብረተሰባችን የተሻለ ኑሮ እንዲኖር ይህ ባህላዊ ለውጥ ከላይ ከጠ ቀስኩት ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መሻሻል ጋር አብሮና ጊዜ ሳይጠብቅ መካሄድ አለበት እላለሁ።

ምንም እንኳን በአብዛኛው የሰዎች ተነሳሽነት መሠረታዊ ግፊቱ የሚመጣው የራስንና የቤተሰብን ኑሮ ለማሻሻል ከሚመነጭ ውስጣዊ ስሜት ቢሆንም፣ በተጨማሪም ውስጣዊ ነፃነትን የሚያጠናክርና ተነሳሽነትን የሚገፋፋ የመንግሥት ፖሊሲና አስተዳደር እንደሚያስፈልግ የማያጠራጥር ቢሆንም፣ ከታሪክ እንደምንማረውና የስነ ልቡና ምሁራንም በተደጋጋሚ እንደሚገልፁት፣ የሰው ልጆችን ድርጊት የሚወስነው በግል ወይንም በቤተሰብ ደረጃ የሚያገኙት ቁሳዊ ጥቅም ብቻ አይደለም። የሰውን ልጅ ድርጊት፣ አብሮ ከመኖር ጋር የተያያዙ ሌሎች ሁኔታዎችም ይገፋፉታል። ከነኝህ ሁኔታዎች ውስጥ በታሪክ በተደጋጋሚ የታየውና ብዙ ሰዎች ህይወታቸውን በመስዋዕትነት እስከመስጠት የሚደርሱበት ጥልቅ ስሜት የአገር ፍቅር ስሜት (Nationalism) ነው። ይህ ስሜት፣ በበጐ ለተጠቀመበት ወገን፣ ግለሰቦችን ለማነሳሳት፣ ማህበረሰብን ለማስተባበርና ጠንካራ አገራዊ ባህልን ለማዳበር ይህንንም ሀይል ለአገር እድገት ለመጠቀም ሁነኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ባጠቃላይ ግለሰቦችን ለስራ ከማነሳሳት በተጨማሪ፣ ለምሳሌ፣ የዚህ ዓይነት አገራዊ ስሜት መዳበር በመንግሥት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ዜጐች ቅንነትንና ለዚያ ዓይነት ስራ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ከግል ጥቅም ያለፈ የጋራና አገራዊ የሞራል ግዴታን ያሸክማል። ይህ ዓይነት ብሔራዊ ስሜት መሠረታዊ ፋይዳ ባይኖረው ኖሮ ይህ የዛሬ ውይይታችን ባልተደረገ ነበር። በኢኮኖሚ እድገት ታሪክ ፈጣን እድገትን በማስመዝገብ የታወቁት አገሮች፣ በሙሉ ማለት ይቻላል፣ ጠንካራ የኢኮኖሚ ብሄርተኝነትን መሠረት ያደረገ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መቅረጻቸው ለእድገታቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። በተለይ እንደኛ ፍፁም ኋላ ቀር ሆነው የተነሱና ከአደጉት አገሮች ላይ ለመድረስ በእጅጉ መሮጥ ያለባቸው አገሮች ኢኮኖሚያቸውን እዚያ ለማድረስ የረዳቸው ሰፋ ባለ አገራዊ ስምምነት ላይ የተመሠረተ፣ ለእድገት ቅድሚያ የሰጠ መንግሥትና  አገርን ለማሳደግ ከተነሳ ውስጣዊ እልህ ጋር የተደባለቀ የኢኮኖሚ ብሄረተኛነትን የተላበሰ አካሄድ ይመስለኛል። ለዚህም ደግሞ ወሰኑን በግልፅ ያወቀ፣ በዚያ ወሰን ክልል ውስጥ የሚኖሩት ህዝቦች ሁሉ እኩልነትና ሙሉ የዜግነት መብት ያላቸው፣ በዚያ ወሰን ክልል ውስጥ የሚቋቋም



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

***መንግሥት ደግሞ በዚያ ወሰን ክልል ውስጥ ያሉ ህዝቦችን በእኩልነት፣ ነገር ግን ከዚያ ወሰን ክልል ውጭ ካሉ ህዝቦች ጋር ሲነፃፀር ደግሞ በተቻለ መጠን አብልጦ የሚያይና እነሱን ከሌሎቹ የሚያስቀድም መሆኑን ማረጋገጥና ህዝቡም ይህን መቀበልና ማመን አለበት፡፡ ይህ ሲሆን የሚፈጠረው አገራዊ ስሜት ሁሉንም የሕብረሰተብ ክፍሎች በየተሰማሩበት የስራ አቅጣጫ ለአገራቸው አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚገፋፉ፣ አንድ አገር እንደ አገር ለመበልፀግ ከሁሉም ዜጎቿ (በአገር ውስጥ ካሉትም ሆነ በውጪ ከሚኖሩት) ልታገኝ የሚገባትን አስተዋፅኦ እንድታገኝ ያደርጋታል፡፡***

***ይህ የት ነው ያለነው ብዬ የሳልኩት ሥዕል በጣም ጨለማ እንደሆነ ይታየኛል፡፡ የተሻለ ህይወት ለመኖር እንችላለን ብየም አምናለሁ፡፡ ይህ እንዲሆን ግን በግልና በጋራ እንደ አገርና እንደ ህዝብ መውሰድ ያለብን ብዙ ቆራጥ እርምጃዎች አሉ፡፡ ይህ እስካልሆነ ግን ውጤቱ ከዚህም ሊብስ እንደሚችል ይታየኛል፡፡***

## III. ስለ ስደት አጠቃላይ

*ምንም እንኳን በጥቅሉ ሲታይ አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ የበለጠ ደስተኛ ሆኖ ለመኖር ተወልዶ ባደገበት፣ ሕዝቡን፣ ባህሉን፣ አኗኗሩን፣ አመጋገቡን በለመደበ**ት** እና በሚያውቅበት፣ በዚህም ምክንያት የባለቤትነት ስሜት* (sense of belonging) *የሚሰማበት አገር እንደሆነ ቢታመንም በተለያየ ምክንያት በትውልድ አገራቸው ያለው ሁኔታ ያልተመቻቸው /ለምሳሌ በፖለቲካ ምክንያት ግን በአብዛኛው በኢኮኖሚ ነክ ጉዳዮች/ ወይንም ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል / በትምህርት ወይንም በስራ/ አገራቸውን ለቀው የሚሰደዱ ሰዎች መኖራቸው የቆየና የተለመደ የሰው ልጆች ድርጊት ነው፡፡ በታራክ እንደ አሜሪካና አውስትራሊያ ያሉ አገሮች የተመሰረቱትም /ቢያንስ አሁን በሚታወቁበት አይነት/ ከተለያዮ አገራት በፈለሱ በእንዲህ አይነት ስደተኞች ነው፡፡*

*የሰዎች አገራቸውን ለቀው መሠደድ ምክንያቱ እንደ አገሩ ሁኔታና እንደጊዜው ይለያያል፡፡ በአገሮች ውስጥ የሚፈጠር የፖለቲካ አለመረጋጋትና ነውጥ የስደት አንደኛው መነሾ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የ1947 የቻይና አብዮት፣ የ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮትና እሱን ተከትሎ የመጣው ያላቋረጠ የፖለቲካ አለመረጋጋት ለብዙ ህዝብ አገሩን ለቆ መሄድ ወይንም ቀድሞ በሌላ ምክንያት ለአጭር ጊዜ ብሎ ለሄደው ላለመመለስ ምክንያቶች መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ በአህጉራችን በአፍሪካ እንደ ሱዳን፣ ኮንጐ ዴሞክራሲዊ ሪፑብሊክ፣ ላይቤሪያና ሶማሊያ*



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

የመሳሰሉ የእርስ በርስ ግጭቶች ለብዙ የየአገራቸው ህዝቦች ወደ ጐረቤት አገሮች መሰደድ ምክንያት ሆነዋል፡፡ የስደት አንድ አይነተኛ ባህሪው ደግሞ ለስደቱ መነሻ የሆነው ምክንያት /በተለይ የፖለቲካና የሲቪል ግጭት/ መፍትሄ ሲያገኝ የተሰደዱት በሙሉ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ ማለት አይደለም፡፡ በተለያየ ምክንያት / የስደትን ኑሮ በመልመድም ጭምር/ የስደት ምንጩ ሲደርቅም በወጡበት የሚቀሩ ሰዎች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ስደቱ የተፈጠረበት ምክንያት ቢፈታም የመፍትሄው አይነትና ይዘት ስላልጣማቸው ሊሆን ይችላል፡፡ /ለምሳሌ ሩዋንዳ፣ ኢትዮጵያ/ መፍትሄውን በአይነቱም በይዘቱም ወደውትም ቢሆን ከመፍትሄው በኋላ በስደት ከለመዱት የኑሮ ሁኔታ ጋር አዲሱን የአገራቸውን ሁኔታ በማወዳደር / ሁኔታው እስኪሻሻል / መሰደድን በመምረጣቸው ይሆናል /ኤርትራ/ ወይም ደግሞ የስደትን ኑሮ በመልመድ አዲሱን ኑሮአቸውን ኑሮ ብለው በመያዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ግን የስደት ምክንያት አንዴ ከተፈጠረ በኋላ ችግሩን ጊዜያዊ ብቻ ነው ብሎ ለማለት ያዳግታል፡፡

ከፖለቲካ ነውጥ ውጪ ምናልባትም በስደት ታሪክ ቅድሚያ የያዘው ከአገር የተሻለ የተመቻቸ የኢኮኖሚ ኑሮ በመፈለግ የሚደረግ ስደት ነው፡፡ በተለይ አዲስ የኢኮኖሚ እድል በአንድ ሁኔታ ሲፈጠር ከዚህ እድል ለመጠቀም ከአገራቸው ካላቸው የኑሮ ሁኔታ ጋር በመመዘን ይህን አዲስ እድል በመጠቀም ኑሮአቸውን ለመደጐም የሚሹ ብዙ ሰዎች አገራቸውን ለቀው ይሄዳሉ፡፡ ከላይ እንደጠቀስኩት በዚህ አይነት የተፈጠሩ አዳዲስ አገሮች በታሪክ ታይተዋል፡፡  በመካከለኛው ምስራቅ የዘይት ሀብት በተገኘበት ጊዜ ከብዙ እስያና አፍሪካ አገሮች ወደዚህ ክፍል አለም የተደረገ ስደት በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ከብዙ የአፍሪካ አገሮች / ኢትዮጵያን ጨምሮ / የተሻለ ኑሮ ለማግኘት ወደ የትኛውም የአለም ክፍል ለመሰደድ የሚደረገው ሩጫ የዚህ አይነቱ ስደት አይነተኛ ባህሪ ነው፡፡

በምንም ምክንያት ይሁን አገራቸውን ትተው የተሰደዱ ሰዎች ከትውልድ አገራቸው ጋር ያላቸው ትስስር /ዜግነታቸውን ከቀየሩ በኋላ እንኳን/ እንዲህ በቀላሉ የሚቆረጥ አይደለም፡፡ ሁሉም ማለት ይቻላል ይብዛም ይነስም በአዲሱ አገራቸው የድሮ አገራቸውን ማህበረሰብ (Community) ይፈጥራሉ፣ እንዳንዶቹ እንዲያውም በስራ ጉዳይ ከሚኖራቸው ግንኙነት ውጪ ሌላው ህይወታቸው በሙሉ ከአዲሱ አገር ህዝብ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ የተወሰኑት ከትውልድ አገራቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት አላቸው፡፡ ፖለቲካውን ይከታተላሉ፣ በአገር ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር በቅርብ ይገናኛሉ፣ በአዲሱ አገራቸው ሆነው በትውልድ አገራቸው ፖለቲካና ማህበራዊ ህይወት ውስጥ በጥልቀት ይሳተፋሉ፡፡ ለተቸገሩ ዘመዶቻቸው ገንዘብ ይልካሉ፣ ለራሳቸውም ለወደፊቱ አገራቸው ሲመለሱ የሚኖራቸውን ኑሮ ለማመቻቸት የመኖሪያ ቤት ይሰራሉ አልፎ አልፎም የንግድ ተቋማት ይፈጥራሉ፡፡



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

በአንዳንድ አገሮች በውጭ ከሚኖሩ ዜጐች የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ የትውልድ አገራቸው ወደውጭ ምርት በመሸጥ ከምታገኘው ገቢ አይተናነስም አንዳንዴም ይልቃል::

**ሠንጠረዥ 1: በተወሰኑ አገሮች በወጭ ከሚኖሩ ዜጐች የሚላክ የገንዘብ መጠን (ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር)**

| *1998 እ.ኤ.አ* | *ኢትዮጵያ* | *ግብፅ* | *ሞሮኮ* | *ሜክሲኮ* | *ዮርዳኖስ* |
|---|---|---|---|---|---|
| *አጠቃላይ ገንዘብ በዶላር* | ***293.4*** | 3,262 | 1,998 | 5,627 | 1335.6 |
| % *ከአጠቃላይ አመታዊ ምርት* | ***4.91*** | ***3.95*** | ***5.55*** | ***1.34*** | ***51.6*** |
| *በነብስ ወከፍ የሚደርሰው* | ***4.89*** | ***53.2*** | ***71.6*** | ***58.22*** | ***212*** |
| ***1999 እ.ኤ.አ*** | | | | | |
| *አጠቃላይ መጠን በዶላር* | 275.1 | 3.195 | 1.918 | 59.09 | 1317.8 |
| % *ከአጠቃላይ አመታዊ ምርት* | ***4.58*** | ***3.6*** | ***5.43*** | ***1.23*** | ***32.5*** |
| *በነብስ ወከፍ የሚደርሰው* | ***4.46*** | ***5.1*** | ***67.9*** | ***60.22*** | ***203.4*** |
| ***2000 እ.ኤ.አ*** | | | | | |
| *አጠቃላይ መጠን በዶላር* | ***374.4*** | 2,817 | 2,138 | 6,572 | 1486.3 |
| % *ከአመታዊ ምርት* | ***5.58*** | ***3.1*** | ***5.91*** | ***1.13*** | ***35.44*** |
| *በነብስ ወከፍ የሚደርሰው* | ***5.9*** | ***44*** | ***74.5*** | ***65.56*** | ***223.2*** |

***ከላይ በሰንጠረዥ 1 እንደሚታየው ከነኝህ ለናሙና ከቀረቡ አገሮች በውጭ ከሚኖሩ ዜጐቻቸው ወደ አገር የሚላከው ገንዘብ እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: ከተጠቀሱት አገሮች ውስጥ በገንዘብ መጠን ወደ ሜክሲኮና ግብፅ የሚላከው ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ ሲሆን የሜክሲኮ በአማካይ በየአመቱ እየጨመረ መጥቶ በ2000 አ.ም ከ6.5 ቢሊዮን ዶላር በላይ የደረሰ ሲሆን የግብፅ ደግሞ እየቀነሰ ከ1998 3.2 ቢሊዮን የነበረው ወደ 2.8 ቢሊዮን ወርዷል:: የሚላከው ገንዘብ በአገሪቱ ላለው ህዝብ በአኩል ቢካፈል እያንዳንዱ ዜጋ ምን ያህል ይደርሰዋል በሚለው እሳቤ ከፍተኛውን ቦታ የምትይዘው ዮርዳኖስ ስትሆን በ2000 አ.ምህረት እያንዳንዱ ዮርዳኖሳዊ ከውጭ ከሚላከው ገንዘብ 223 ዶላር ይደርሰዋል ይህም ከአገሩ አመታዊ የነብስ ወከፍ ገቢ እሩቡን ይሆናል:: በዜጐች ከውጭ የሚላከው ገንዘብ ምንም እንኳን እያደር እየጨመረ ቢሆንም በመጠኑም፣ በነብስ ወከፍ ክፍፍሉም እጅግ ዝቅተኛ የሆነው የኢትዮጵያ ሲሆን በጣም ትልቅ በነበረበት በ2000 ዓ.ም አጠቃላይ መጠኑ 374 ሚሊዮን፣ የነብስ ወከፍ ድርሻው ደግሞ ወደ 6 ዶላር ብቻ ነው:: ይህም ሆኖ ግን በኢትዮጵያ እንኳን ይህ መጠን አገሪቱ***



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ወደውጭ እቃ በመላክ ከምታገኘው ከግማሽ በላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ ይህ የሚያሳየው በውጭ የሚኖሩ ዜጐች ለትውልድ አገራቸው የኢኮኖሚ ገፅታ ላይ የሚኖራቸው ሚና ቀላል እንዳልሆነ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በትውልድ አገር የሚገኙ የመንግሥት ባለሚሎች ይህን ሀብት ይንከባከባሉ፡፡

ሌሎች ደግሞ ቁሳዊ በሆነ መልኩ ይህ ነው የሚባል ትስስር ባይፈጥሩም የትውልድ አገራቸውን በትዝታቸው ይዘው  አቅም በሚፈቅድላቸው ጊዜ ወይንም የተለየ አጋጣሚ ሲፈጠር ወደ ትውልድ አገራቸው ለአጭር ጊዜም ቢሆን ተመልሰው ትዝታቸውን ያድሳሉ፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ ለአገራቸው የውጭ ምንዛሪ ያስገኛሉ፡፡

የሰዎች ከአገራቸው መፍለስ በአገራቸው ላይ የሚፈጥረው እንድምታም እንደ አገሩና እንደ ሁኔታው ይለያያል፡፡ አንዳንድ አገሮች የህዝባቸውን መፍለስ ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው አንፃር በመመልከት ሥርአት ባለው መንገድ አደራጅተው ያስኬዱታል፡፡ ለሌሎች ደግሞ የህዝብ መፍለስ በተለይ የኑሮ ሁኔታው ከተሻሻለው አካባቢ (ከተማረው ክፍል ለምሳሌ) በሚሆንበት ጊዜ አገሪቱ እድገት ላይ የሚያመጣውን ችግር በመመልከት ስደቱን ለመግታት ይጥራሉ፡፡ በአጠቃላይ ስደት እንደ አገሩ ሁኔታ፣ እንደ ጊዜውና እንደሚመለከተው የህብረተሰብ ክፍል ለአንድ አገር እድገት አጋዥም እንቅፋት ፈጣሪም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም ነው ስለ ስደትና እድገት ስናወራ ጥቅምና ጉዳቱን በጥቅሉ ከማውራታችን በፊት የአገሩን ሁኔታ ጠለቅ ብለን መመልከት የሚኖርብን፡፡

በኢትዮጵያ ስደት (በተለይ እንዲህ በተጠናከረ መልኩ) የአጭር ጊዜ ታሪክ ነው ያለው፡፡ አገርን ለቆ መሄድ እንደ ነውርና ሀፍረት ከሚቆጠርበት ጊዜ አገር ውስጥ መኖር እንደ ጅልነት እስከሚቆጠርበት ጊዜ (በተለይ በወጣቶች)  ያለፉት ከሶስት አስርት አመታት እምብዛም አያልፍም፡፡ ምንም እንኳን በተለይ በስራ ፍለጋ ምክንያትና በትምህርት ፍለጋ በቅድመ አብዮት ዘመን መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን በውጭ አገር ቢኖሩም በተለይ በፖለቲካ ምክንያት (ይህም ፖለቲካው የፈጠረውን ሽብር በመሸሽ የወጣውን ይጨምራል) አገር ጥሎ መሄድ በሰፊው የጀመረው በደርግ ዘመን መሆኑ ብዙ አያከራክርም፡፡ ይህ በደርግ ዘመን በሰፊው የተጀመረ የፖለቲካ ስደት ግን እራሱን ከሌላው ደብቆ ይኖር የነበረውን የኢትዮጵያን ህዝብ ከሌላው አለም ጋር በሰፊው አስተዋውቆታል ማለት ይቻላል፡፡ ልጆቹን ከደርግ በትርና ብሄራዊ ውትድርና ለማሸሽ «የቻለው በቦሌ ያልቻለው በባሌ» ማንቀሳቀስ የጀመረው በተለይ የአገሪቱ ልሂቅ ስደትን ቀስ በቀስ እየተላመደውና እየወደደው ሄዶ በውጭ አገር የተሰደዱ ልጆች ብዛት( በዚያ



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

አገር ምንም ይሰሩ ምን) ቀስ በቀስ ለቤተሰብ የመጦሪያ ተቀማጭ ሂሳብ አልፎም የስኬት መለኪያና መኩራሪያ መሆን ከጀመሩ ሰንበትበት ብሏል:: የፖለቲካ ሁኔታው ትንሽ ከተረጋጋም በኋላ ቢሆን በአገሪቱ የተንሰራፋው ሰፊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር በደርግ ጊዜ ለተጀመረው የፖለቲካ ስደት ተጨማሪ ነዳጅ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ ምናልባት የተቀባይ አገሮች እያደር እየጠበቀ የሄደው የቪዛ እገዳ ይቀንሰው ካልሆነ በቀር ስደት ለኢትዮጵያውያን ሊያቆሙት የማይቻል ጉርፍ ሆኖአል:: ይህ እውነት ከሆነ ዘንዳ በአጠቃላይ ስደትንና በተለይ ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት የሚደረግ ውይይት ትርፋማ ሊሆን የሚችለው ውይይቱን በሁለት መልክ ማስኬድ ስንችል ይመስለኛል ይኸውም:

(1) በአጠቃላይ አገርን ጥሎ መሰደድ በአገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ላይ የሚያመጣውን ተፅእኖ በሰከነ መንፈስና በዝርዝር መመልከትና በተለይ ከፉ ጉዳት ያመጣሉ በሚባሉት ላይ በሰፊ አገራዊ ውይይት ላይ የተመሠረተ መፍትሄ መፈለግ:-

(2) በአንድ መክንያትም ሆነ በሌላ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እድገት ሊያደርጉ የሚችሉትን አስተዋፅኦ በጥሞና በመመልከት ባላቸው አቅምና ፍላጐት ላይ በመመስረት ከፍተኛውን አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉበትን መንገድ ማስላትና ይህንንም ማመቻቸት

ምንም እንኳን በእኔ እምነት ከላይ በተ.ቁ. አንድ ላይ የተነሳውን ጥያቄ በሚመለከት ያለኝ አስተያየት እያደር አሉታዊ እየሆነ የሄደ ቢሆንምና በተለይም ስደት የችግሮች ሁሉ መፍትሄ እየሆነ መታየቱና ይህም እየፈጠረ ያለው ስነ ልቡና ለወደፊት እድገታችን አደገኛ እንቅፋት እየሆነ ይሄዳል የሚል እምነት ብይዝም፣ በዚህ ላይ ያለኝን አመለካከት ለጊዜው አቅቤ የዛሬው ውይይት በአብዛኛው እንዲያተኩር ወደተፈለገበት ከላይ በ2ኛ ተ.ቁ ወደ ተነሳው ጥያቄ ልመለስ::

## IV. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ለአገር እድገት የሚኖራቸው ሚና

እንግዲህ የአገራችን መሠረታዊ ችግሮችና የሚታዮኝን አጠቃላይ የመፍትሄ ሃሳቦች በሚመለከትና **ስለስደት አጠቃላይ ሁኔታ ያለኝን ግንዛቤ ለመንደርደሪያ ያህል አቀረብኩ** በእኔ ግምት ለዚህ ለዛሬ ውይይታችን ዋነኛ ወደሆነውና ወደ መጨረሻው የፅሁፌ ክፍል ልግባ:: አሁን አገራችን ላለችበት ሁኔታና ከላይ በእኔ ግምት ለችግሮቿ



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

መንስኤ ባልኳቸው የአስተሳሰብ፣ የአስተዳደርና የካፒታል ችግሮች ላይ በትንሹም ቢሆን ስምምነት ካለን ቀሪው ጥያቄ ታዲያ ይህንን ችግር ለመቅረፍ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሚና ምንድን ይሆናል? የሚለው ይሆናል:: በእኔ እምነት ይህን ጉዳይ በሚመለከት የሚደረጉ ውይይቶች ብዙ ጊዜ የሚስቱት ነገር ያለ ይመስለኛል:: ይኸውም በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በሙሉ በአንድ ጉተራ ውስጥ በመክተት ለሁሉም አንድ አይነት ሚና ማዘጋጀት ነው:: እንደ እኔ ለረጅም ጊዜ ውጭ አገር ለኖረና የውጭውን የኢትዮጵያውያን ኑሮ ለተከታተለ እንዲህ አይነት አመለካከት ስህተትነቱ ብቻ ሳይሆን በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አገሪቱ ልታገኝ የምትችለውን ሰፊ ጥቅም እንዳታገኝ ያደርጋታል የሚል እምነት አለኝ:: ስለዚህም ለዚህ ውይይት እንዲረዳ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ለኢትዮጵያ ሊሰጡ ከሚችሉት ጥቅምና ለአገሪቱ እድገት ሊኖራቸው ከሚችለው ሚና አንፃር **ብቻ** መለያየቱ አስፈላጊ ነወ ብዬ አምናለሁ:: ወደዚህ ምደባ ከማምራቴ በፊት ግን በአጠቃላይ በመርህ ደረጃ ሊታሰቡ የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦችን አስቀምጬ ልለፍ-:

(1) በውጭ የ**ሚ**ኖሩ ኢትዮጵያውያን ለአገር እድገት የ**ሚ**ኖራቸውን ሚና መቀበልና ይህንንም መጠቆም በምንም አይነት ስደትን ማበረታታት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባዋል:: በተለይ በአሁኑ ጊዜ የስደቱ ቅጥ ማጣት በተለይ የአገሪቱን የተማረ የሰው ሀይል በእጅጉ እያመነመነው መሄድ፣ ይህም የአገራችንን የወደፊት እድገት ፍፁም እየተፈታተነው እንደሆነና፣ ከዚያም በላይ ግን ለመሰደድ ያለው ፍላጎት በአገር ውስጥ በሚኖረውም ነዋሪ ዘንድ እየፈጠረ ያለው የግዴለሽነትና የጊዜያዊነት ባህሪ (በትምህርት፣ በስራ፣ በማህበራዊ ኑሮ... ወዘተ) እጅግ አደገኛና የእድገት ፀር መሆኑ ሁላችንንም ሊያሳስብ የሚገባ መሆኑ-:

(2) አገራችን ካለባት መጠን የለሽ ችግር አንፃር በውጭ ከሚኖሩ ሁሉም አይነት ኢትዮጵያውያን እንደ ኢኮኖሚ አቅማቸው፣ እንደ እውቀታቸውና ችሎታቸው ሊያበረክቱ የሚችሉትን ማንኛውንም ቀና አስተዋፅኦ መጠቀም እንደሚገባና **ለዚህም መጣር እንደሚያስፈልግ**

(3) ይህም ሲሆን ግን በምንም መልኩ አካሄዳቸው ከላይ የኢትዮጵያ ችግሮች ብዬ የዘረዘርኳቸውን የሚያባብሱ ሆነው ከተገኙ ቢያንስ እነኝህ በያዙት መንገድ እንዳይበረታቱ መከላከል ይገባል:: በውጭ የ**ሚ**ኖር ወይም የኖረ ሁሉ " ጥሩ" ነው ወይንም " አወንታዊ ሚና ይጫወታል " የሚል ጭፍን የዋህነት ሊኖር አይገባም በመጨረሻም



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

(4) ልክ የውጭ አገር ኢንቬስተሮች ለመሳብ በሚደረገው ጥረት " ትርፋማነት " ዋና መሳቢያው እንደሆነ ሁሉ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለአገር እድገት እንዲያበረክቱ ዋና መገፋፊያው የአገር ፍቅርና ከአገር ጋር ያለ ትስስር ነው፡፡ ስለሆነም በመንግሥት በኩል የአገር ፍቅርን እያዳከሙና እያኮሰሱ በውጭ ካለው ኢትዮጵያዊ ይህን ጥቅም መጠበቅ ተላላነት ነው፡፡ ስለዚህም በአገር ውስጥ ያለው መንግሥት ኢትዮጵያዊ ብሄረተኛነትን ማሳየት ይገባዋል፡፡

በጥቅሉ በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በአገር እድገት ለማሳተፍ የሚያስፈልጉ ጉዳዬችን በሚመለከት ይህን ያህል ካልኩ፡፡ ይህን ጥቅም ለማግኘት የሚያስፈልጉ ዝርዝር ጉዳዬች ውስጥ ልግባ፡፡ በመጀመሪያ ከላይ እንዳልኩት አገሪቱ የምትፈልገው ድጋፍ **ከላይ ያነሳኋቸውን ሶስት** ችግሮቻችንን የሚቀርፉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ እያንዳንዱ በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ደግሞ በነኝህ በሶስቱም ጉዳዮች ላይ ችሎታ ወይም ብቃት አለው ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህም የመጀመሪያው ተግባር መሆን ያለበት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት ለውይይት የሚረዳ ምደባ (Category) መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በእኔ እምነት ለውይይታችን እንዲረዳ በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ስድስት ጥቅል ምደባዎች ማካተት ይቻላል፡፡

ሀ) በተለያየ ምክንያት ከለፍላጎቱ (ከኢኮኖሚ ችግሮች ውጪ) ከአገር የወጣና ቢችልና ሁኔታው ቢመቻችለት አገሩ መመለስና ለአገሩ እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ የሚፈልጉ **ግን "ምን ይዤ ልግባ" የሚለው በጣም የሚያስጨንቅ፡፡**

ለ) በተለያየ ምክንያት አገሩ መመለስ የማይችል ወይም የማይፈልግ ግን ውጪ ብዙ ከመቆየት ብዛት ስፋ ያለ እውቀት ያዳበረ (በተለያየ ሙያ)፣በተጨማሪም የአገሩ ውድቀት የሚያበግነውና በአለው ሙያ (ኑሮው በፈቀደው መጠን) አገሩን ለመርዳት በጣም የሚፈልግ፣ ሆኖም ግልጋሎቱን በኢትዮጵያ ካለው መንግስት ጋር በጥብቅ የሚያያይዝ (አገርን መርዳት መንግስትን መረዳት ነው ብሎ የሚያስብ)

ሐ) ከላይ በ (ለ) እንደተጠቀሰው ሆኖ ግን የመንግስት ማንነት ብዙ የማያሳስበውና በሙያው ብቻ መርዳት የሚፈልግ **ግን በምን መልክ መርዳት እንደሚችል ያላወቀ ወይንም ሁኔታው ያልተመቻቸለት**



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

መ) በውጭ አገር ንብረት ያፈሩ፣ ካላቸው ንብረት በመጠኑም ቢሆን የተወሰነውን በአገራቸው ኢንቬስት ማድረግ የሚፈልጉ ሆኖም (መ-1) ይህን ማድረግ መንግሥትን ማጠናከር የሚመስላቸው ወይም (መ-2) **ስለ** መንግሥት (ፖለቲካ) ብዙም ግድ የሌላቸውና ግን አገር ውስጥ ስላለው የቢሮክራሲ ሁኔታ ከሚሰሙት ብቻ በመፍራት ወደ አገር ኢንቬስት ማድረግን የሚሸሹ

ሠ) ኢትዮጵያን ለኑሮ የማይመኟት፣ ለችግሯም ብዙ የማያስቡ ግን ለትዝታዎ የሚፈልጓት፣ ስለሆነም በተቻለ መጠን ባገኙት ጊዜና ኑሮአቸው በሚፈቅደው መጠን እየተመላለሱ ሊያዩት የሚፈልጉ፣ በተለይም በችግራቸው ጊዜ (ለሀዘን) ወይንም ለደስታ (ለሰርግ) አገራቸውን (ዘመዶቻቸውን) የሚፈልጉ:: ቢችሉ የጡረታ እድሜያቸው ሲደርስ አገራቸው ገብተው ማረፍ የሚፈልጉ ይህም ግን በሁለት ሊከፈል ይችላል አንድም ለኑራ የሚፈልጓት ሌላም ዝምብለው ለትዝታዋ:-

ረ) ከወጡ ጀምሮ ሕይወታቸውን ለኢትዮጵያ ፖለቲካ የሰጡ፣ የ**ኢ**ትዮጵያን **የአስተዳደር ስርዓት** ጥሩ ነው ብለው በሚያስቡት መልክ ለመቀየር የሚሹ (ለዚህም በውጭ ሆነው የሚታገሉ) ከነኝህም ግን

1) ለራሳቸው ምንም የፖለቲ**ካ** ስልጣን ፍላጎት የሌላቸው ግን የአ**ገ**ሪቱ ዋነኛ ችግር **የአስተዳደር ስርዓት** መጥፎነት ነው ብለው የሚያስቡ ስለዚህም ይህን ለማስተከከል የራሳቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያምኑ:-
2) አገሪቱ ያለ እነሱ መፍትሄ እንደማይኖራት እርግጠኛ የሆኑና የእነርሱ ስልጣን አከባቢ መኖር ምንም ምርጫ የሌለው ብቸኛ መፍትሄ ነው ብለው የሚያምኑ:: ለዚህም ለጊዜው አገሪቱን ጎዳም አልጎዳም ወደ ስልጣን ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንቅፋት ነው ብለው የሚያስቡትን ሁሉ ለማስወገድ የሚታገሉ::

ይህን አመዳደብ ሙሉ በመሉም ባይሆን (ከዚህም የዘረዘረ አመዳደብ ማውጣት ይቻላል) በመጠኑ ያስኬዳል ብለን ከተቀበልን ከዚህ የሚቀጥለው እንግዲህ ይህን **ሃይል** ለአገር እድገት እንዴት መጠቀም እንችላለን የሚለው ነው:: ከላይ በዝርዝር እንደተጠቀሰው አገሪቱ ልትከተለው የሚገባት እስትራቴጂ እነኝህ የተለያዩ ዜጎች ያላቸውን አቅምና ችሎታ የመዘነና ለእያንዳንዱ ክፍል የተለያዮ አካሄዶች የቀየሰ ሊሆን ይገባል:: **በመነሻ የአገሪቱ ችግሮች ያልኳቸውን ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች** በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ አይነት ከዘረዘርኩበት ምደባ (Category) ጋር **ማዛመድ** ጥሩ አቅጣጫ አመላካች ይመስለኛል::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

በጣም ከሚቀለው ልጀምር:: አብዛኛው በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ በነኚህ ሶስት የኢትዮጵያ ችግሮች ዙሪያ ብዙ አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል ብዬ ስለማምን አስተዋፅኦቸው አሉታዊ ይሆናል ከምለው ልጀምር:: እነኚህ ከላይ ከመደብኳቸው ውስጥ በተለይ ሁለቱን ይመለከታል እነኚህም::

1) ኢትዮጵያን ለጉራ ብቻ የሚፈልጋትና ይህንንም ለማድረግ በተለይ በአገሪቱ ያለውን " የአሠተሳሰብ " ችግር ከመቅረፍ ይልቅ ሊያባብሱ የሚችሉ ሀይሎች (ይህንን የሚያደርጉት ግን ሆን ብለው ለመጉዳት ላይሆን ይችላል)
2) የአገሪቱ **የአስተዳደር ስርዓት** ያለእነሱ ስልጣን ላይ መውጣት መፍትሄ እንደሌላው የሚያምኑ ለዚህም የአገሪቱን ዘላቂ ጥቅም ጉዳም አልጎዳም፣ ወደ ስልጣን ሊመውጣት **ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንቅፋት ነው ብለው የሚያስቡትን ሁሉ ለማስወገድ የሚታገሉ ፣ ለዚህም ውሸትን ፣ ቅጥፈትን ፣ አሉባልታን፣ ሽብር መንዛትን፣ ስም ማጥፋትን የትግል ስልት አድርገው የሚጠቀሙ::**

**እነኝህ ሁለት አይነት ኢትዮጵያውያን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አገሪቱ ውስጥ ላለው ችግር መፍትሄ ከማስገኛት ይልቅ ችግሩን በማባባስ የሚጫወቱት ሚና የላቀ ነው:: ከመጀመሪያው አይነት ኢትዮጵያውያን አንድ ምሳሌ ለአብነት ልጥቀስ (ሌሎች ብዙ ምሳሌዎች ማሳየት ይቻላል) ሰርግ::**

**በኢትዮጵያችን ያለ አንድ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ችግር አቅምን አውቆ አለመኖር ፣ በተለይም በጣም ጊዜያዊ ለሆኑ ባህላዊ ኩነቶች (ለደስታ፣ ለሀዘን፣ ወዘተ) ያለንን ጥሪት አሟጦ መጠቀምና ይህ ሁኔታ ሲያልፍ እራስንና ቤተሰብን አጉል የሆነ የኢኮኖሚ ችግር ውስጥ መክተት ነው:: ለሰርግ ተብሎ ያለን ንብረት ሸጦ አገር ምድሩን መጋበዝ ፣ ተዝካር አወጣለሁ ብሎ የማረሻ በሬውን ማረድና ለዘላለም ከድህነት ጋር መቆራኘት… ወዘተ በጣም ስር የሰደደ መጥፎ ባህል፣ ለእድገት የሚያስፈልገንን ካፒታል በከንቱ ማባከን መሆኑን በአገር ውስጥ እንኳን ያሉ ሽማግሌዎች ህብረተሰቡን በየጊዜው የሚገሰፅበትና በአንዳንድ አካባቢዎችም (ለምሳሌ በገጠሩ የጉራጌ ክፍል) ማህበረሰቡ ተሰብስቦ ውሳኔ ያሳለፈባቸው ጉዳዮች ናቸው:: እንግዲህ ይህ አላዋቂ የሚባል ህብረተሰብ እንኳን ፍሬ ከርስኪነቱን አምኖ ለመተው የሚታገልባቸውን እነኝህን ኋላ ቀር ባህሎች አወቀ፣ መጠቀ ተብሎ የሚባልለት፣ እንደነኚህ አይነት ወጪዎች (በተለይ ከመጠን ሲያልፍ) ጭራሽ እንደ ጅልነት በሚቆጠሩበት አገሮች እየኖሩ ለጉራ ሲባል**



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ብቻ እራሳቸው ከሚኖሩበት አገር አልፌው ኢትዮጵያ ድረስ መጥተው የኔ ወይስ ያንቺ ድግስ ይበልጣል ብሎ ፉክክር ምን የሚሉት አማርኛ ነው? በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንደሰርግ አይነት የተለየ የደስታ ጊዜአቸውን በአገራችው ለምን መጥተው አሳለፉ አይደለም:: ነገር ግን ስንት ደክመው ያፈሩትን ትንሽ ሀብት በፍጽም በህይወታቸው አይተዋቸው የማያውቋቸውን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አግበስብሰው ማበላትና ፣ በዚህም መኩራስ በፍጽም ቅጥ ያጣ ግብዝነት ነው:: አንዳንድ በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በእንዲህ አይነት ግብዝነት ለእንዴት አይነት የኢኮኖሚ ችግር እንደሚዳርጉ ይታወቃል:: ሌላው ቢቀር ይህ ወደፊት ለሚወልዷቸው ልጆች አለማሰብ ነው:: ጉራው ከመጡበት አገር ላሉ ወዳጆቻቸው ከሆነ እዚያው ባሉበት ቢያደርጉት ይሻላል:: ለአገራችን ችግር "የአስተሳሰብ ለውጥ" እጅግ ያስፈልጋል በምንልበት በአሁን ጊዜ በውጭ ቆይታቸው ይህንን ግብዝነት ይዘውልን የሚመጡት ግን አገሪቱን እየረዱ ሳይሆን እንዲያውም እየጎዱ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል::

በሁለተኛ ደረጃ ያስቀመጥኩት ግን ከዚህም የከፋ ችግር የሚያስከትሉ ናቸው:: ችግሩ ደግሞ መጠን ሰፊ ነው:: የመጀመሪያው ስህተት በብዙ ሺህ ማይሎች ከአገር ርቆ በአገር ለሚመጣ ለውጥ ዋነኛው ወኪል እኔ ነኝ ብሎ ማሰብና ከልብ ማመኑ ቢያንስ እራስን አንቱ የማለት ለከት የሌለው የበላይነት ስሜት ሲበዛም በስነ ልቡና ሃኪም ሊታይ የሚገባው ሁነኛ የአዕምሮ መዛባት ይመስለኛል:: ሁለተኛ እንደዚህ በርቀት ሆኖ ለውጥ ለማምጣት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በተቻለ መጠን በድርጊት የሚያሳያቸው ብዙ ተምሳሌቶች ሊኖሩ ይገባል:: በተለይም እንደነኝህ አይነት ሀይሎች በአብዛኛው የሚገኙት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በሰፈነባቸው የምዕራብ አገሮች እንደመሆኑ ከዚያ የፖለቲካ ልምድ በመቅሰም ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚጠናከርበትን መንገድ፣ መቻቻልን፣ መደማመጥን የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ አካሄዶችን በማሳየት በአገር ውስጥ ያለውን ብዙ ማስተማር ሲገባ ይብሱኑ ፍጽም በውሸትና በማደናገር ላይ በተመሰረተ፣ እጅግ ጊዜው ባለፈበት (በኢትዮጵያ እንኳን) የበሬ ወለደ ፖለቲካ በውጭ የሚኖረውን አልፎ በአገር ውስጥ ያለውን ህዝብ ነገ ውሸትነቱ በሚታወቅ ከንቱ ፕሮፓጋንዳ ለማደራጀትና በዚያ አቋራጭ ስልጣን ላይ ለመንጠላጠል መባዘን ከአፍራሽነቱም በላይ በፍፁም በጤንነት የሚታይ አይደለም:: በእኔ እምነት ከአሁን በኋላ (እንደ ከዚህ በፊቱ) በአገራችን ለውጥ የሚመጣ ከሆነ (ለውጥ መምጣት እንደሚያስፈልግ ከላይ ገልጨዋለሁ) በአገር ውስጥ ባሉ ሀይሎችና በማህበረሰቡ ሰፊ እንቅስቃሴ ብቻ ነው የሚሆነው:: ከዚያም በላይ፣ ለአገራችን ጤናማ ኑሮ የምንመኝ ከሆነ ዘንዳ ሊመጣ የሚገባው ለውጥ ሰላማዊና ብዙው የህብረተሰብ ክፍል መብቴን አስከብራለሁ ብሎ



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

**የሚነሳበት አይነት እንቅስቃሴ ነው፡፡ ስለዚህ እንደነኝህ አይነት ሀይሎች ምንም እንኳን ቁጥራቸው በጣም አናሳ ቢሆን በእምነታቸው አክራሪነት ምክንያት ሊያደርሱ የሚችሉትን አደጋ ከወዲሁ በመገንዘብ፣ ሲሆን ይበልጥ አወንታዊ የሆነ የፖለቲካ አካሄድ የሚይዙበትን** ካልሆነም ግን ከዚህ አፍራሽ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ በአገር ውስጥም ባሉ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችም ሆነ በውጭ በሚኖሩ አብዛኛው ኢትዮጵያዊያን በማያወላዳ መንገድ ሊገለፅላቸው ይገባል፡፡ "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" ፖለቲካ ኢትዮጵያ አሁን ላለችበት "የአስተዳደር ችግር" በምንም መልኩ መፍትሄ አይሆንምና ! **ሙሉ ጊዜዬን አገሪቱ የፖለቲካ ለውጥ ለማምጣት ማዋል እፈልገለሁ ለሚል ግን ይህ መብቱ ብቻ ሳይሆን በዚህም አገሩን መጥቀም ይችላልና ሊበረታታ ይገባዋል፡፡ ይህንን ማድረገ የሚቻለው ግን በአገር ውስጥ ብቻ ነውና አገራችሁ ገብታችሁ ይህንን አድርጉ እላለሁ፡፡** አሉታዊ ሚና ይጫወታሉ ባልኳቸው ላይ በጥቂቱ ይህን ካልኩ ይበልጥ አወንታዊ ሚና ሊጫወቱ በሚችሉት በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ላይ በማተኮር ንግግሬን ላብቃ::

በመጀመሪያ፣ በተለያየ ምክንያት ከአገሩ ውጪ መኖር የማይፈልገውና ቢመቸው አገሩ ተመልሶ መኖርና መስራት የሚፈልገውን በሙሉ የሚመለስበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል:: በርግጥ አገሪቱ አሁን ባለችበት ሁኔታ ለእንደዚህ አይነት ሰዎች ሁሉ የተዘጋጀ ስራ ላይኖራት ይችላል:: ሆኖም በአብዛኛው እንዲህ አይነት ሰዎች ተቀጥረው ለመስራት ሳይሆን መመለስ የሚፈለጉት ወይንም በሙያቸው አሊያም እራሳቸውን ለማስተዳደር የሚያስችል አነስተኛ ስራ ይዘው ነው አገራቸው መግባት የሚፈልጉት:: በተለይ በአውሮፖ አሁን ባለው " ፀረ ስደተኛ " ስሜት ምክንያት አንዳንድ የአውሮፖ አገሮች እንዲህ አይነት ሰዎች ወደ አገራቸው ሲመለሱ ለመቋቋሚያ የሚሆን አነስተኛ ካፒታል ለመስጠትም ፈቃደኞች ሆነዋል:: እነኝህ ኢትዮጵያውያን በተለይ በኖሩበት አገር ያለውን የሥራ ስሜት ( work ethic ) ከልባቸው ከያዙት ባለቻቸው ትንሽም ጥሪት ቢሆን ኢትዮጵያ መጥተው ሊሰሩ፣ ንብረት ሊያፈሩ ምናልባትም ለሌሎች ዜጎች የሥራ እድል ሊፈጥሩ ይችላሉ:: በተለይ ጠንካራ የስራ ባህል ያላቸው ከሆኑና **ምንም ይሁን ምን ያላቸውን ሙያ ከምር ከወሰዱት** በአገራችን ያለውን የሥራ መንፈስ በመቀየር በኩል ሁነኛ አስተዋፅኦ የሚኖራቸው ይመስለኛል::  ይህንንም ለማገዝ በየአገሩ ያሉ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ማህበራት ሁነኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ::

በሁለተኛ ደረጃ ያለው ለረጅም ጊዜ በውጭ በመኖር ብዙ እውቀትና የሥራ ልምድ ያካበተውን ይመለከታል:: ይህ ሀይል በጣም ብዙ ሚና ሊጫወት የሚችል ግን



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

እስከአሁን በቅጡ ያልተጠቀምንበት ሀይል ነው:: በመጀመሪያ ከዚህ ሀይል ውስጥ ብዙው ለማለት ይቻላል ኢትዮጵያን "በምንም መልኩ መርዳት መንግሥትን መርዳት ነው" በሚል አገርንና መንግሥትን በማይለይ የተዛባ አመለካከት የተወናበደውን ወደ ትክክለኛ አስተሳሰብ መመለስ ይገባል:: ይህም በጣም ከባድ ሊሆን አይገባም:: አንድም ይህ አስተሳሰብ ሀሰት የሚሆንባቸው ብዙ ምሳሌዎች ማሳየት ይቻላል:: ለምሳሌ ብዙ ሙያተኞች ከመንግሥት ጋር ብቻ ሳይሆን ከመንግሥት ውጪ ያሉ የየሙያ ማህበራት ጋር የእውቀት ልውውጥ ሊያደርጉ ይችላሉ:: ይህን በማድረጋቸውም መንግሥትን አለማጠናከራቸው ብቻ ሳይሆን መንግሥትን የሚቋቋሙ ጠንካራ የሙያ ማህበራት እንዲኖሩና እንዲጐለብቱ ሊረዱ ይችላሉ:: ይህም ማለት ኢትዮጵያ ከመንግሥት ጋር ያልተነካኩ ብዙ የሲቪል ማህበረሰብ አካላት ያሉባት አገር እንደመሆኗ መንግሥትን መሸሽ ለሚፈልጉ ባለሙያዎች ብዙ እድሎች አሉ:: በሌላ በኩል ግን በጊዜያዊነት መንግሥትን ይረዳልና ይህ ከሚሆን ህዝቡ ይጐዳ የሚል አስተሳሰብ ( ለምሳሌ በረሀብ የተጐዱትን ከመርዳት ዝም ብሎ መቀመጥ) በጣም ከጠባብ ስሜት የመነጨ በህዝብ ህይወት ቁማር የሚጫወት አስተሳሰብ ብቻ ነው የሚሆነው::

ይህንን የመጀመሪያውን መሰናከል ካለፍን በኋላ ግን በውጭ የሚኖሩ የተማሩና ባለሙያ ኢትዮጵያውያን ለአገራችን እድገት በሁሉም መስኩ ሊያደርጉ የሚችሉት አስተዋፅኦ በፍፁም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህ እውቀት ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገሮች ለማደግ እጅግ ከሚያስፈልጓቸው ነገሮች ዋናዎቹ ናቸው:: ብዙ ኢትዮጵያውያን በጤና፣ በትምህርት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በሳይንስ ...ወዘተ መስክ ስመጥር በሆኑ በውጭ አገር ተቋሞች ይሰራሉ:: ይህን እውቀትና የስራ ልምድ አገራቸው ለሚገኙ መሰል ባለሙያዎች ቢያስተላልፉት አገሪቱ እንዲህ በቀላል የማይሰላ ጥቅም ነው የምታገኘው:: በእነኝህ ሙያተኞች ለመጠቀም እነኝህ ሰዎች ወደ አገራቸው መመለስ የለባቸውም፣ ባሉበት ቦታ ሆነው ለትውልድ አገራቸው ብዙ ሊሰሩ ይችላሉ:: ይህ እንዲሆን ግን በውጭ በሚኖሩትም፣ አገር ውስጥ ባሉትም ኢትዮጵያውያን ትንሽ ጥረት ያስፈልጋል:: አገር ውስጥ ያሉት ሙያተኞች በውጭ ካሉ ወገኖቻቸው ለመጠቀም እንዲቻል ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል:: በተለይም እነኝህ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሙያተኞች ሁልጊዜ ስለ ኢትዮጵያ እንዲያስቡና በዚህም ዙሪያ ጥናት እንዲያዘጋጁ መወትወት ያስፈልጋል:: በአገር ውስጥ በአመት አንድ ጊዜ የሚደረጉ የሙያ ማህበራት አመታዊ ኮንፍረንሶች ለዚህ አይነተኛ መሳሪያ ሊሆኑ ይችላሉ:: በመንግስትም ሆነ በግል የትምህርት ተቋማት በተወሰነ ጊዜ የረጅም ጊዜ እረፍታቸውን ሲወስዱ አገራቸው መጥተው ለጥቂት ወራት የሚሰሩበትን መንገድ ማመቻቸት ሌላው



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

መንገድ ነው፡፡ አገሪቱ ውስጥ ባሉት አገራዊ የንግድ ተቋማት ወይንም አገራዊ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ለጥቂት ሳምንታትም ቢሆን እያመጡ ልምዳቸውን ቢያካፍሉ ወይንም ዝም ብለው አብረው ቢሰሩ እነሱም በአገሪቱ ስላለው የንግድ ችግር ይማራሉ አገር ውስጥ ያሉ ተቋማትም በሌላው አገር ያለውን አሰራር ይማሩበታል፡፡ ሌላ ቀርቶ አገራቸውን በጣም በወጣትነታቸው የለቀቁ ወይንም እዚያ የተወለዱ ወላጆቻቸው ኢትዮጵያውያን የሆኑ **ወጣቶች** ትምህርታቸውን ገና የጨረሱና ለመጨረስ የተዳረሱ ተማሪዎች የሁለት ወር የክረምት እረፍት ግዚያቸውን አገራቸው መጥተው በአገር ካሉ ተቋማት ጋር በልምምድ ( Internship ) መልክ ቢሰሩ የአገራቸውን ችግሮች በቅርቡ እንዲያዮ ከዚያም ከአገሪቱ ጋር ያላቸውን ትስስር ሊያጠናክሩ ይችላሉ፡፡ በተለይ በህክምና ዘርፍ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያን (አብዛኞቹ ማለት ይቻላል በአገራቸው የነፃ ትምህርት ተምረው የሄዱ) ለትውልድና ላስተማራቸው አገር አገልግሎት የመስጠት የሞራል ሃላፊነትም ጭምር ሊሰማቸው ይገባል፡፡ ብዙዎቹም ይህ ስሜት የሚሰማቸውና በተቻላቸው አገራቸውን የሚያገለግሉበ**ት** መንገድ ቢፈጠር የሚፈልጉ ይመስለኛል፡፡ ሁኔታውን ማመቻቸት ከተቻለም ጠቀሜታው መሠረታዊ ነው የሚሆነው፡፡ ለምሳሌ ያክል በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የህክምና ባለሙያዎች በግልም ሆነ በስብስብ ( በግሩኘ ) በአመት አንድ ጊዜ ለተወሰነ ጊዜ ( ለሳምንታት ) ኢትዮጵያ እየመጡ አገልግሎት ሰጥተው ሊመለሱ ይችላሉ፡፡ ከተባበሩና ከጉበዙ ይህንን ግልጋሎት ሊሰጡ የሚችሉባቸው መሳሪያዎች እዚያው በእርዳታ ማግኘት የሚችሉ ይመስለኛል፡፡ በአገር ውስጥ የሚገኙ የሙያ ጓደኞቻቸውና መንግሥት ሲመጡ የሚሰሩበትን ቦታ፣ ካስፈለገም መኖሪያ በቋሚነት ሊያዘጋጁላቸው **የሚችሉ ይመስለኛል**፡፡ እነኝህ ለአብነት የጠቀስኳቸው የትብብር መስኮች በጣም ጥቂ**ቶቹ** ናቸው፡፡ ቅን ልቦናው ካለና ለአገራችን የጋራና ውስብስብ ችግሮች በረጅሙ ማየት ከቻልን ያለ ብዙ ወጪ ለአገሪቱ ዘላቂ ጥቅም የሚያስገኙ ብዙ፣ እጅግ ብዙ ነገሮች ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር አመታዊ ኮንፍረንሱን ከአምና ጀምሮ አለማቀፍዊ ያደረገውና በተለይም በክረምቱ መግቢያ ላይ ያደረገው ሆን ብ**ሎ** እንዲህ አይነቱን የእውቀት ልውውጥ ለማበረታታት ስለሆነ የአገሪቱን እድገት በሚመለከት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ የሚባሉ ማናቸውም የምርምር ውጤቶች (በተለይ በኢኮኖሚክስና በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ) በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዲቀርቡ በጣም **ያ**በረታታል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ያለው ምንም አከራካሪ ያልሆነው ነው፡፡ ይኸውም በውጭ አገር በመኖር ንብረት ያፈራው ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ይህ እስከአሁን ካለው መረጃ በቁጥር በጣም አናሳ የሆነ ግን ሊኖረው የሚችለው አስተዋፅኦ አይነተኛ ነው፡፡ እ**ዚ**ህ ላይ ሊታይ የሚገባው



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

እነኝህ ባለሀብቶች ከሌላው ባለሀብት ጋር ሲታይ እጅግ የላቀ ካፒታል ስላላቸው አይደለም ( ምናልባት በጣም ከጥቂቶች በስተቀር ):: ነገር ግን አገሪቱ ካለባት የውጭ ምንዛሪ እጥረት አንፃር ሲታይ፣ እነኝህ ሰዎች ካላቸው የውጭ ትስስርና ግንኙነት (Contacts) ፣ ስለ አለም አቀፍ የንግድ ማእቀፍ የሚኖራቸው እውቀትና በዚህም ማእቀፍ ውስጥ ተወዳድሮ ለማሸነፍ ስለሚያስፈልጉ የንግድ አሰራሮች ያላቸው ተመክሮ ለአገሪቱ ትልቅ እሴት አለው:: የኢትዮጵያ መንግሥት ለእድገታችን ወሳኝ የውጭ ኢንቬስትመንት ነው በማለት የውጭ ኢንቬስትመንት አገር ውስጥ ለማስገባት ሲዳክር ይኸው አስር አመታት አለፉ:: ምንም ይሽ ነው የሚባል የውጭ ኢንቬስትመንት አልመጣም:: በተደጋጋሚ በአገር ውስጥ ውይይቶች ለማቅረብ እንደሞከርኩት ይህ በፍፁም ሊገርመን አይገባም:: ከሌሎች አገሮች እንማር ካልን (ቪየትናም፣ ቻይና፣ ህንድ ... **ወዘተ**) ትርፍ ፍለጋ የሚመጣ የውጭ ሀብት በመጀመሪያ በዚያ አገር ይህ ነው የሚባል የእድገት እንቅስቃሴ መኖሩን ሲያይና ሲያምን ነው ወደዚያ አገር ካፒታል የሚያፈሰው:: ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ግን በመጀመሪያ በአገር ውስጥ የሚኖረው ባለሀብት፣ ከዚያም በውጭ የሚኖሩ የአገሩ ዜጐች ስለአገሪቱ የወደፊት ህይወት ብሩህ ተስፋ ሊኖራቸውና ይህንንም ተስፋቸውን ያላቸውን ንብረት በማሰራት ሊያሳዮት ይገባል:: እነኝህ ሁለት ሀይሎች ደግሞ ከውጪው ባለሀብት ይልቅ ይህንን ለማድረግ የሚቀድሙት አንድም ስለአገሪቱ የበለጠና የጠለቀ እውቀት ስላላቸው በዚህም ለውጭው ባለሀብት " አብሪ " ሆነው ሊያገለግሉ በመቻላቸው ሌላም ከትርፍም በላይ አገራዊ ስሜት ስለሚኖራቸው ነው:: ስለዚህም ነው ካፒታል ከውጭ እንዲመጣለት የሚፈልግ መንግሥት ከምንም በላይ ይህንን ሀይል ሊንከባከብ የሚገባው::

ይህንን ሀይል ማንቀሳቀስ ግን እንዲህ በቀላሉ "መኪና ከታክስ ውጪ ታስገባለህ " በሚል የሚዘልቁት አይደለም:: ለማግባባት የሚሞከረው ኪሱን ብቻ ሳይሆን ብሄራዊ ስሜቱን በመኮርኮር እስከሆነ ዘንዳ ያንን ብሄራዊ ስሜቱን ለማነሳሳት የሚያስችሉ ከወሬ ያለፉ ሁነኛ እርምጃዎች በተግባር ሲወሰዱ ብቻ ነው ይህ ሊሆን የሚችለው:: ከዚህ ውስጥ አንዱን (አጠቃላይ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን) ለዚህ ክፍል ብቻ ሳይሆን በጥቅሉ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ከላይ ጠቅሼዋለሁ:: ከዚህም በላይ ግን የንብረት ዋስትና፣ የአገሪቱ ህዝብ ( የራሱን ጨምሮ ) የሰብአዊ መብቶች መከበር፣ መልካም አስተዳደር መኖር፣ በአብዛኛው ህዝብ ተቀባይነት ያለው ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት፣ የሚሰራ የፍትህ ስርአት ... ወዘተ እንዲህ አይነቱን ከአገሪቱ ጋር ጥብቅ የሆነ የስሜትና የማህበራዊ ትስስር ላለው በውጭ ነዋሪ አስፈላጊ ይመስለኛል:: እነኝህ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት፣ ከዚህ ክፍል ሊገኝ የሚችለው የካፒታልም ሆነ የልምድ አስተዋፅኦ በእጅጉ አናሳ ሲሆን



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ይታየኛል። የእነኝህ ነገሮች መስተካከል በእርግጥም ጥቅሙ ከዚህም በላይና መጠነ ሰፊ መሆኑን ቀደም ብዬ በዝርዝር ጠቅሼዋለሁ። በጠባቡ ስናየው እንኳን የነኝህ ሁኔታዎች በቅጡ አለመስተካከል ሊፈጥሩ የሚችሉትን እንቅፋቶች ለማመላከትና ለማስረገጥም ነው።

በአራተኛው ምደባ ያስቀመጥቁት አንድ ወጥ ያልሆነ በጣም የተወሳሰበ በጥቅሉ "ሰፊው ስደተኛ" ተብሎ ሊቀርብ የሚችል ነው። ምናልባትም ስገምተው አመልማል አባተ "ምነው **ልቤን ስደት ስደት አለው**" ብላ የዘፈነችለት ክፍል ነው።

ይህ ክፍል የአገር የኢኮኖሚ ሁኔታ ጨለማ ሆኖበት የተሻለ ኑሮ ፍለጋ የወጣ፣ ከአዲሱ አገር የእለት ተ**ዕለት** ኑሮ ጋር ግብግብ የገጠመ፣ ኑሮውን ለማሸነፍ ሲወጣ ሲወርድ የሚውል ስለዚህም በትውልድ አገሩ ያለውን ሁኔታ በቅርቡ ለመከታተል ጊዜውም፣ ጉልበቱም የሌለው (እንደው የተለየ ሁኔት ካልተፈጠረ በቀር) ግን ከስራ ወጥቶ ሲዝናና ቢፈልግ ያገሩን ልጆች የሚፈልግ፣ ቤቱ ሲገባ ወይንም ከስራ ወደ ቤቱ ሲሄድ በመኪና ውስጥ የአገር ዘፈን (ወይንም ሌሎች ቀልዳ ቀልዶች) የሚሰማ ስለዚህም የውስጥ ስሜቱ በፍፁም ከአገሩ ያልተለየ፣ አቅ**ሙ** በፈቀደ መጠን አገሩ እየተመላለሰ ትዝታውን ማደስ የሚፈልግ፣ በህይወት ዘመኑ ካሉት ትልቅ አላማዎች አንዱ (ምናልባት ዋነኛው) አንድ ቀን የኢኮኖሚ ሁኔታውን በደንብ አመቻችቶ ሲሆን ቀደም ብሎ ካልሆነም ቢያንስ ጡረታውን አስከብሮ፣ ትን**ሽ** ገንዘብ ቋጥሮ፣ ጥሩ ቤት በአገሩ ሰርቶ መኖር የሚፈልግ በዚህ በጡረታ ዘመኑም ዝም ብ**ሎ** መኖር ሳይሆን ስለግል ኢኮኖሚ**ው** ብዙ ሳይጨነቅ ለትውልድ አገሩ ትንሽም ብትሆን አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚፈልግ ነው።

ይህ ሀይል እውነተኛው እምቅ የአገር ሀይል ነው። ምናልባትም ባልሳሳት ከላይ በሰንጠረዥ አንድ ላይ በውጭ ከሚኖሩ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው ገንዘብ በጣም አብዛኛው ከዚህ ሀይል በአገር ያሉ የተቸገሩ ዘመዶች ለመርዳት የሚላክ ገንዘብ ይመስለኛል። ይህ ደግሞ በእኔ ግምት ገና ምንም ያልተነካ እምቅ ሀብት ነው። **ከዚህ እምቅ የሰውና የገንዘብ ሃይል አገሪቱ በሰፊው ልትጠቀም ትችላለች**። ይህን ለማድረግ ግን በመጀመሪያ ይህንን የአገር ስሜትና ትዝ**ታ** እንዲቀጥል መደረግ አለበት። ከዚህም በላይ ግን ይህ ህዝብ የወደፊት ህይወቱን ኢትዮጵያ ለመኖር ያለውን አላማ በሰፊው ማበረታታት ይገባል። ይህንን ካመነና ለተግባራዊነቱም ከተንቀሳቀሰ ሌላው ቀርቶ ለራሱ አንድ የመኖሪያ ቤት ቢሰራ በዚህ ምክንያት ወደ አገር የሚገባው የካፒታል (የውጭ ምንዛሪ) መጠን በራሱ ብቻ እስከአሁን ወደ አገራችን የሚገባውን ጠቅላላ የውጭ



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ካፒታል ፍሰት በእጅጉ ይልቃል፡፡ እንዲሁ በኤንቬሎኘ ጀርባ በሚደረግ ትንሽ ስሌት ለማሳየት ያክል አሁን በውጭ አገር (በበለፀጉ አገሮችና በአረብ አገሮች) የሚኖረው ኢትዮጵያዊ አምስት መቶ ሺህ ግድም ነው ብንልና (ከዚህ እንደሚልቅ ብዙ ማስረጃዎች አሉ) ከዚህ ውስጥ ግማሹ ብቻ እንኳን በጡረታ ጊዜው አገሩ ለመመለስና ለመኖር ስለዚህም በአገሩ ቤት መስራት ይፈልጋል ብንል፣ ይህ በአገሩ ለመስራት የሚፈልገው ቤት በአማካይ 50,000 የአሜሪካን ዶላር ያወጣል ብንልና ይህ ህዝብ በሚቀጥሉት 30 አመታት ውስጥ የጡረታ እድሜው ደርሶ (በተለያየ ጊዜ) ጡረታ ይወጣል ብንል ይህ ወደ አገሪቱ የሚያስገባው የካፒታል ፍሰት በ30 አመት 12.5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወይንም በአመት ወደ 417 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገደማ ነው፡፡ ይህም አገሪቷ በአሁኑ ጊዜ የምታገኘውን የውጭ ኢንቬስትመንት (የሚድሮክን ጨምሮ) አራት አምስት እጥፍ ይሆናል፡፡ በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣውም ለውጥ ቀላል አይሆንም፡፡ ከሚገኘው ገንዘብ በላይም ግን የዚህ አይነት ስሜት በኢትዮጵያውያን መሰረፁ ሰፊ ፋይዳ ያለው ይመስለኛል፡፡ እንዲህ አይነት ተጨባጭ ንብረት በትውልድ አገራቸው ሲኖራቸው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ጋር የሚኖራቸው የፖለቲካ የባህልና የእውቀት ትስስር በዚያው ልክ መሬት የረገጠ ይሆንና በሌላው መስክ የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ የበለጠ ያጎላዋል፡፡

በመጨረሻ በአጭሩ ጠቅሼ የማልፈው ስደተኛ ኢትዮጵያዊ የአገሪቱ የአስተዳደር ስርዓት የሚያሳስበው፣ የዚህ ሁኔታ መስተካከል ለአጠቃላይ የአገሪቱ እድገት ወሳኝ መሆኑን የሚያምን በተለይም አገሪቱ የሰዎች መብት የሚከበርባት፣ ፍትህ የሰፈነባት፣ መንግስት በህዝቧ ቁጥጥር ስር የሆነባት አገር እንድትሆን ማየት የሚሹ ቅንና አገር ወዳድ ኢትዮያውያን ነው፡፡ እነኝህ ሰዎች ማንም በካፒታልም ሆነ በእውቀት ከሚያደርገው አስተዋፅኦ በላይ ለአገራቸው ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ ከላይ እንደጠቀስኩት የአገራችን አንድ ዋና ችግር የአስተዳደር በተለይም የውስጥ ነፃነት ማጣት ነው፡፡ ይህንን ለመቅረፍ በአገር ውስጥ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በውጭ የሚኖሩ ኢትዮያውያን ከፍተኛ የሞራልና የትብብር ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በአገሪቱ የሰብአዊ መብቶች ሲጣሱ በአለም አቀፍ ደረጃ ድምፃቸውን በማሰማት ያጋልጣሉ፣ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር በሰፊው እንዲመሰረት (የምርጫን ፍትሃዊነት፣ የሚዲያን ነፃነትና ገለልተኝነት... ወዘተ) በሚኖሩባቸው አገሮች ባሉ መንግስታት በኩል ግፊት ያደርጋሉ ፣ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲጠናከሩ አስፈላጊ ናቸው በሚሏቸውና ከውጭው አገር ልምድ በመነሳት ትምህርታዊ ፅሁፎችን ያዘጋጃሉ ይህንንም በአገር



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ውስጥ ለሚኖረው ህዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች ያሰራጫሉ። ይህ ሁሉ በጣም ሰፊ ፋይዳ ያለው ስራ ነው። ጥቅሙም የአጭር ጊዜ ሳይሆን የረጅም ጊዜ ፣ የተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን ከመደገፍና ከመቃወም ይልቅ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ሂደቱን ለመርዳትና ይህንን ሂደት ለማደናቀፍ በሚሞክሩ ሁሉም አይነት የፖለቲካ ሃይሎች ላይ ያነጣጠረ በትር መሆኑ ሰፋ ያለ ድጋፍና በአገር ውስጥ ተቀባይነት ያጎናፅፈዋል። ምክንያቱም ወገናዊነቱ ለፖለቲካ ድርጅቶች ሳይሆን ለአገርና ለዴሞክራሲታዊ ስርዓት ስለሚሆን። እንዲህ አይነት ሰፊና የተቀናጀ እንቅስቃሴም በትውልድ አገራቸው ብቻ ሳይሆን በሚኖሩበት አገርም ያሉን የፖለቲካ ሃይሎች ለዚህ ጉዳይ ለማሳተፍ የሚቀላቸው ይመስለኛል።

## ማጠቃለያ

እንግዲህ ከላይ ዘርዘር አድርጌ ለማሳየት እንደሞከርኩት አገራችን ያለችበት ሁኔታ አሳዛኝና ከሁሉም ዜጎች ድጋፍንና ትብብርን የምትሻበት ጊዜ ነው። የችግሮቹ መፍትሄዎች በጥቅሉ የአስተሳሰብ የአስተዳደርና የካፒታል እንደሆኑ በጥቅሉ ለማሳየት ሞክሬአለሁ። በዚህ ዙሪያ ከዚህም ዘርዘር ያሉ ብዙ ነገሮች ማለት ይቻላል። እነኝህ ሀሳቦች ለውይይት መነሻ የቀረቡ እንደመሆናቸው ሌሎች ወገኖች የበለጠ አስበውበትና ተጨንቀውበት ከዚህም የበለጠ ለእውቀታቸን የሚረዳ ዝርዝር ሀሳቦች ይዘው እንደሚቀርቡ ተስፋ አለኝ።

እነኝህን ችግሮቻችንን ለመፍታት በአገር ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ትልቁን ሚና እንደሚጫወቱ ምንም ጥርጥር የለኝም። ሆኖም ግን ለብቻቸው በቀላሉ የሚወጡት ችግር ሳይሆን በውጭ ከሚኖሩ ወገኖቻቸው ጋር በመተባበር ብቻ ነው ሊያደርጉት የሚቻላቸው። ይህ እንዲሆን ግን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮያውያንን በአንድ ስልቻ እንዳለ ድንች አንድ ወጥ አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ ትንሽ አፍታቶ ማየት ይጠቅማል በሚል ለዚሁ ጥቅም እንዲውል ብቻ በታሰበ ምደባ ለመመደብ ሞክሬአለሁ። በነገራችን ላይ ይህ አይነት ምደባ በተቀናጀና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በደንብ ቢሰራ (በተለይ ውጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን) በጣም ብዙ እውቀት የሚያስጨብጠንና ስለሆነም ሰፊ ፋይዳ ያለው ይመስለኛል። ከዚህ ምደባም በመነሳት አገሪቱ እንዴትና በምን መልኩ በውጭ ከሚኖሩ ዜጎቿ ልትጠቀም እንደምትችልና እንደሚገባት ለማመላከት ሞክሬአለሁ።



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ይህ አቀራረብ በትንሹም ቢሆን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮያውያን ይጎነትላል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡ ምክንያቱም ይህ ጉንተላ የሚያስነሳው ክርክር፣ ይህ ክርክር የሚገፋፋው ዝርዝር ጥናት፣ ከእነኚህ ጥናቶች በመነሳት የሚደረጉ ሌሎች ውይይቶች ከዚያ በኋላ (አንዳንዴ አገራችን እንዳለው ማለቂያ የሌላው የዘወትር ሰብሰባ እንዳይሆን) የሚወሰዱ የድርጊት እንቅስቃሴዎች ናቸው ለምንወዳት፣ በህሊናችን ሁሌ የምናስባት ግን ከአለሙ ሁሉ ወደ ኋላ እየቀረች ላስቸገረችንና፣ አንዳንዴ ለምታሳፍረን አገራችን ሁለት እርምጃ ወደፊት እንድትራመድ ከከንፈር መምጠጥ ያለፈ አስተዋፅኦ ልናደርግላት የሚያስችለን፡፡

አመሰግናለሁ



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com